# እኔነቱ

(አብርሃም   በየነ)

ሻንቅላ ጃንጅሮ ጉርጂ ልሁን አፋር፣

ሸዋ ልሁን ወሎ ከፋ ልሁን ሀረር፣

ኦረሚፋ ይሁን ትግርኛ ልናገር፣

ቢሻይ ልሁን ወይጦ አማራ ኩናማ፣

አኘዋክ ጉራጌ አገው ወይ ሲዳማ፣

ልምሰል ጥቁር ከሰል ወይም የቀይ ዳማ፣

ቋንቋየና ዘሬ ቢጨምር ብዛቱን፣

እንደ ነብር ቆዳ ዥንጉርጉርነቱን፣

ከቶ አይለውጠውም የኔን እኔነቱን፣

ብሎ የተሰዋው ተሰፋየ ደብሳይ፣

ታሪኩን አኑሯል ከመቃብር በላይ!

እልፍ ኣእላፍ ወጣት ሽማግሌ አሮጊት፣

ምሁር ወይም በርጌስ የገበረው ህይዎት፣

በቋንቋው በዘሩ በዞጉ በዕምነቱ፣

እንደ ነብር ቆዳ ዥንጉርጉርነቱ፣

ኢትዮጵያዊነቱ የጌጥ ፈርጡ ሆኖ፣

ፍትህና ሰላም ዕኩልነት ሰፍኖ፣

በነጻነት ሸማ መኖር ተዘባኖ፣

ዜጋ በሃገሩ በልቶ ማደር ጠግቦ፣

ዕድል እንዳያገኝ ሴራ ተሸርቦ፣

ዘር ሳይዙ መሬት.... ነገሩ ሆነና፣

በባዕዳን ዕረዳት ክህደት በንግስና፣

የዚያን ትውልድ ፈርጥ የነጻነት ፋና፣

የደብተራውን ህልም የቁርጡን ቀን ጀግና፣

ዕምነትና ጽናት ኢትዮጵያዊነቱን፣

ዘብ ቆሞ ይጠብቅ ሁሉም ዕኔነቱን!!

ህዳር 2000 ዓ.ም

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com